የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፸፱
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 79
ADDIS ABABA 8th November, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፰/፪ሺ፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ………………………………………………………ገጽ ፯ሺ፮፻፺፯

CONTENTS

PROCLAMATON No. 858 /2014

Ethiopian Broadcasting Corporation Establishment Proclamation…………………………..………..Page 7697

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፰/፪ሺ፮

## የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የብሮድካስት አገልግሎት ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየተሻሻለ በመምጣቱ ይህንኑ በአግባቡ ተጠቅሞ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያለውን የብሮድካስት አገልግሎት አደረጃጀትና አሠራር ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የሀገሪቱን ልማት፣ ሠላምና ዲሞክራሲ እና የሕዝቦቿን በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ አንድነት አጠናክሮ ለማስቀጠል የብሮድካስት አገልግሎት ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ፤

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን መንግሥትና ሕዝብን በማገናኘት የሕዝቡን የልማት ተሳታፊነትና የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ መወጣት እንዲችል እና በህብረተሰቡ መካከል ሐሳቦችና አመለካከቶች በሕገመንግሥቱ በተደነገገው መሠረት በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የተቋምና የአሠራር ነፃነት እንዲሁም የተሻለ የሕግ ጥበቃ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION No. 858/2014

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF ETHIOPIAN BROADCASTING CORPORATION

WHEREAS, the broadcasting service technology has grown and renovated from time to time; and subsequently, it is found necessary to improve the existing organizational structure and procedure of broadcast service by putting appropriate utilization of the same technology into place inorder to ensure the benefits of the society;

RECOGNIZING, THAT, the role of broadcast service is highly significant in further strengthening and ensuring the sustainable continuity of development, peace and democracy of the country and democratic unity of the society which is founded on equality and liberal integration;

WHEREAS, it is found necessary that Ethiopian Radio and Television has its own institutional and procedural freedom as well as better legal protection so as to discharge its expected role in serving as bridge to connect the government and the people thereby ensuring civic participation and common benefit of the society and promote free expression of ideologies and views among the society in compliance with the provisions of the Constitution;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 12.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን በማቋቋም ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት የበለጠ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፰/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ሠራተኛ" ማለት የኮርፖሬሽኑ ጋዜጠኞች፣ የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ ዳይሬክተሮችና በተዋረድ ያሉ የሥራ ኃላፊዎችን ያካትታል፤

፪/ "ብሮድካስቲንግ" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅ ወይም ለማዝናናት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት እና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካኝነት የሚከናወን የድምጽ እና የምስልና የድምጽ ስርጭት ነው፤

፫/ "ቦርድ" ማለት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ አባላትን የያዘ ኮርፖሬሽኑን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፤

፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፭/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፮/ "ፕሮግራም" ማለት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ የሚቀርብ ስርጭት ነው፤

WHEREAS, it is found necessary to establish Ethiopian Broadcasting Corporation and enable it to provide its service in a more efficient, quality and competent way;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Broadcasting Corporation Establishment Proclamation No. 858/2014".

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation፡

1/ "employee" includes journalists, technical staffs, supportive staffs, directors and hierarchal officials of the Corporation;

2/ "broadcasting" means audio and audio-visual broadcasting service delivered to the public in order to educate, inform or entertain the society through radio, television, internet and different electronic devices;

3/ "Board" means a body that is responsible to hold steering management responsibility of leading the Corporation comprising members appointed by the House of Peoples' Representatives upon recommendation by the Prime Minister;

4/ "region" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city Administrations;

5/ "person" means any natural legal person;

6/ "program" means vocal or visual or audiovisual arrangement transmitted to inform, educate or entertain or all-inclusive transmission program;

፯/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

### ፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ “ኮርፖሬሽን” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

### ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በመላ አገሪቱ እና በውጭ አገራት በተለያዩ ሥፍራዎች ቅርንጫፎች እና ወኪሎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

### ፭. የኮርፖሬሽኑ ዓላማ

የኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች፡-

፩/ በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ስለሚፈጸሙ አበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች እንዲሁም ትምህርታዊና አዝናኝ ዝግጅቶችን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድረ-ገጽ በማቅረብ፤ ከሕዝቡም በግብረ-መልስ ሥርዓት ወይም በቀጥታ የሚገኘውን ግብዓት በመጠቀም ሕዝቡ በአገሪቱ በሚካሄዱ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ኖሮት በአገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ፤

፪/ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር አገራዊ ማንነትን፣ ብዝሃነትን፣ መቻቻልንና ዲሞክራሲያዊ አንድነትን ለመጠበቅና ለማጎልበት የሚደረገውን አገራዊ ጥረት ማገዝ ይሆናል፡፡

### ፮. የኮርፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ለሕዝብ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ዜናዎችና መዋዕለ-ዜናዎችን ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀትና በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድረ-ገጽ በልዩ ልዩ የአገር ውስጥና የውጭ ቋንቋዎች በማሠራጨት ለተገልጋዩ የማድረስ፤

7/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## ETHIOPIAN BROADCASTING CORPORATION

### 3. Establishment

1/ The Ethiopian Broadcasting Corporation (hereinafter “the Corporation”) is hereby established as an autonomous government institution having legal personality and rendering public service.

2/ The Corporation shall be accountale to the House of Peoples’ Representatives.

### 4. Head Office

The head office of the Corporation shall be in Addis Ababa and it may have branches and agents at different places locally and abroad as may be necessary.

### 5. Objective of the Corporation

The objectives of the Corporation are:

1/ broadcasting main and current issues happening in the country and abroad as well as educational and entertainment events on the radio, television and website in compliance with mass media and other relevant laws and utilizing feed backs in the form of feedback receiving system or direct input coming from the public thereby enhance the awareness of the public on overall activities carried out in the country and become active participant in the development of the country;

2/ creating national consensus; supporting all national efforts made to protect and promote national identity and dignity, diversity, tolerance and democratic unity.

### 6. Powers and Duties of the Corporation

The Corporation shall have the following powers and duties:

1/ to collect news and news packages which are relevant and important for the society and deliver them to the beneficiaries on the radio, television and website in different local and foreign languages;

፪/ ለልማት፣ ለመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ግንባታ ህብረተሰቡን የሚያነሳሱ ትምህርታዊና አሳዋቂ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ሕጎች ለሕዝብ የማስተዋወቅ፤

፫/ ሕዝቡ ስለ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር የሚረዱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

፬/ ነጻ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ የማስተላለፍ፤

፭/ የሕዝቡን ዕውቀትና ፈጠራ የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

፮/ በአገር ውስጥና ከውጭ ካሉ ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የመመሥረት፤

፯/ ለክልል ብዙሃን መገናኛ ድርጅቶች የቴክኒክና ሥልጠና ድጋፍ የመስጠት፤

፰/ ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ የመወሰንና የመሰብሰብ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በከፊል ወይም በሙሉ ከክፍያ ነፃ የማድረግ፤

፱/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

፲/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን።

፯. የኮርፖሬሽኑ አቋም

ኮርፖሬሽኑ፡-

፩/ ቦርድ፤

፪/ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና አስፈላጊ የሆኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፤

፫/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

፰. ስለቦርዱ

፩/ ቦርዱ አንድ ሰብሳቢ፣ አንድ ጸሐፊና ሰባት አባላት ያሉት ሆኖ የአባላቱ ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ይችላል።

፪/ የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው ተቋማ

2/ to present educational and informative programs that mobilize the public towards development, good governance and building democratic system; to introduce government policies and laws to the public;

3/ to broadcast programs that help the society to build awareness regarding human and democratic rights;

4/ to receive and broadcast free public comments and disclosures;

5/ to present various programs that may build up the knowledge and innovative career of the public and satisfy its entertainment demands;

6/ to create relations with similar domestic and foreign agencies;

7/ to provide technical and training supports to regional mass – media agencies;

8/ to determine and collect service charges, and exempt partially or wholly as may be necessary;

9/ to own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

10/ to perform other related activities so as to achieve its objective.

7. **Organizational Structure of the Corporation**

The Corporation shall have:

1/ a Board;

2/ a Chief Executive Officer and the necessary Deputy Chief Executive Officers;

3/ the necessary staffs.

8. **The Board**

1/ The Board shall comprise a chairman, a secretary and seven members, save this number may increase as it may be necessary.

2/ The chairperson and members of the Board, who have been drawn from pertinent

ትና ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተውጣጥተው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡

፫/ የቦርዱ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

፬/ የቦርዱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

፭/ ዋና ስራ አስፈጻሚው የቦርዱ ጸሐፊና አባል ይሆናል፡፡

፮/ ቦርዱ የራሱ የአሠራር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ መገናኛ ብዙሃንን በሚመለከቱ የመንግሥት ፖሊሲ ዎች እና ሕጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

፪/ በህዝብ መታወቅ ያለባቸው የመንግሥት ፖሊሲዎ ችና ሕጎች በወቅቱ መተላለፋቸውን የማረጋገጥ፤

፫/ ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ሕዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የመገምገም፣ ይበልጥ ተጠቃሚ ስለሚሆን በት ሁኔታ ሐሳብ የማቅረብ፤

፬/ የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፍትሐዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የማረጋገጥ፤

፭/ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔትና በሌሎች በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን ፕሮግራም ይዘት የመገምገም፣ ስለሚሻሻልበትም ሁኔታ ሐሳብ የማቅረብ፤

፮/ ከአድማጭና ከተመልካች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመመርመር፣ ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት፤

፯/ የኮርፖሬሽኑን ሠራተኞች የቅጥር መመሪያ የማው ጣት፣ ደመወዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞቻቸው ላይ የመወሰን፤

institutions and different classes of society, shall, upon recommendation by the Prime Minister, be appointed by House of Peoples' Representatives.

3/ The Board shall be accountable to the House of Peoples' Representatives.

4/ The term of the Board shall be five years.

5/ The Chief Executive Officer shall be the secretary and member of the Board.

6/ The Board shall issue its own working rule.

**9. Powers and Duties of the Board**

The Board shall have the following powers and duties፡

1/ to ensure that government policies and laws pertinent to mass media are put into practice in the Corporation;

2/ to ensure that the Corporation has timely disseminated and broadcasted government policies and laws that need to be publicized to the society;

3/ to evaluate whether or not the public is benefited from the service provided by the Corporation; to present recommendations as to how the public becomes further beneficiary;

4/ to ensure political parties and classes of society with different views are given balanced radio and television service fairly;

5/ to evaluate the contents of the program broadcasted on the radio, television, internet and other electronic devices and to forward recommendations on the ways of improve ment;

6/ to assess and investigate complaints presented by audiences and spectators against the Corporation; to give appropriate decision;

7/ to draw up employment directive for the staffs of the Corporation; determine salary, allowance and other benefits;

፰/ ኮርፖሬሽኑ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ የመቀየስ፤

፱/ የኮርፖሬሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ እቅስቃሴ ሪፖርት ገምግሞ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፤

፲/ ኮርፖሬሽኑን በሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የመምከር፤ የመወሰን፡፡

## ፲. የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

፪/ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ቢያንስ አንድ ሶስተኛው አባላት ከጠየቁ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፫/ በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፬/ ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሐሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

፭/ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. ስለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

፩/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማል፡፡

፪/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኮርፖሬሽኑን ሥራ ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው፡-

8/ to design ways to further strengthen the Corporation and improve its procedures;

9/ to evaluate the annual action plan and budget as well as work performance report of the Corporation and present them to the House of Peoples' Representatives;

10/ to deliberate and make decision regarding other policy issues related to the Corporation.

## 10. Meetings of the Board

1/ The Board shall conduct regular meeting at least once a month.

2/ In case of emergency, the Board may hold a session at any time if the chairperson or at least one-thirds of members so request.

3/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at its meeting.

4/ Decision of the Board shall be passed by majority vote; and incase of a tie, the chairperson have a casting vote.

5/ The Board may adopt its own rules of meeting procedure.

## 11. The Chief Executive Officer of the Corporation

1/ The Chief Executive Officer, shall, upon recommendation by the Prime Minister, be appointed by the House of Peoples' Representatives.

2/ The Chief Executive Officer shall be the Chief Executive Officer of the Corporation and shall carry out the duties of the Corporation with the overall direction from the Board.

3/ Without prejudice to the generality of the provision of sub article (2) of this Article, the Chief Executive Officer shall:

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ለኮርፖሬሽኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፕሮግራሞች ይዘት አቅጣጫን ያቅዳል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

ሐ) የኮርፖሬሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

መ) የኮርፖሬሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሠ) ለኮርፖሬሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮርፖሬሽኑን ይወክላል፤

ሰ) ከቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፬/ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ለኮርፖሬሽኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ሆኖም እርሱን ተክቶ የሚሠራው ከሠላሳ ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

## ፲፪. ስለምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች

፩/ የኮርፖሬሽኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት በቦርዱ ይሾማሉ፡፡

፪/ እያንዳንዱ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ ከዋናው ሥራ አስፈጻሚ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በሥሩ የተመደበለትን ዘርፍ ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ እንዲሁም ከዋና አስፈጻሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፫. ሪፖርት ስለማቅረብ

ኮርፖሬሽኑ በሥልጣን ክልሉ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት በየጊዜው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

a) exercise the powers and duties entrusted to the Corporation under Article 5 of this Proclamation;

b) plan, followup and supervise the contents of the programes direction;

c) hire and administer the employees of the Corporation.

d) draw up annual action plan and budget as well as work progress report of the Corporation and present them to the Board;

e) effect expenditure in accordance with the annual budget and work plan approved for the Corporation;

f) represent the Corporation in all its dealings with third parties;

g) perform other tasks assigned to him by the Board.

4/ The Chief Executive Officer may partially delegate his powers and duties to officials and staffs of the Corporation to speed up the performance to extent necessary for the efficient performance of the activities of the Corporation; nevertheless, if the delegation is going to last for a period exceeding thirty days, such delegation should be submitted to the Board and authorized accordingly.

## 12. Deputy Chief Executive Officers

1/ The Deputy Chief Executive Officers, shall, upon recommendation by the Chief Executive Officer, be appointed by the Board.

2/ Each Deputy Chief Executive Officer shall manage, coordinate his department tasks based on the direction provided to him by the Chief Executive Officer; as well as, carry out other tasks assigned to him by the Chief Executive Officer.

## 13. Reporting

The Corporation shall submit to the House of Peoples' Representatives periodic report regard ing the tasks it performs within the limit of its power.

**፲፬. የኮርፖሬሽኑ በጀት**

የኮርፖሬሽኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰብ ገቢ፤

፪/ ለኮርፖሬሽኑ ዓላማ መሳካት ሲባል መንግሥት ከሚያደርግለት ድጋፍ፤

፫/ ከሌሎች ምንጮች፡፡

**፲፭. ስለኮርፖሬሽኑ የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት**

የኮርፖሬሽኑ የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

**፲፮. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ኮርፖሬሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትና የገንዘብ ሰነዶች ይይዛል፡፡

፪/ የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**ክፍል ሦስት**
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፲፯. ስለኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች አስተዳደር**

የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች አስተዳደር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይመራል፡፡

**፲፰. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ቦርዱ ለዚህ አዋጅ ማስፈጸሚያና ለተለያዩ የኮርፖሬሽኑ አሠራሮች የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣል ይችላል፡፡

**፲፱. የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**

የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

**14. Budget of the Corporation**

The budget of the Corporation shall be drawn from the following sources:

1/ revenues collected in accordance with this Proclamation;
2/ supportive budget that may be allocated to the Corporation by government in order that the Corporation achieves its objectives;
3/ other sources.

**15. Procurement and Financial system**

The procurement and financial system of the Corporation shall be governed by the procurem ent and financial system of public enterprises.

**16. Books of Account**

1/ The Corporation shall keep complete and accurate books of accounts and financial documents.

2/ The books of accounts and financial docum ents of the Corporation shall be audited annually by the Auditor General.

**PART THREE**
**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**17. Administration of Employees**

The administration of the employees of the Corporation shall be governed by regulation to be issued by the House of Peoples' Representatives.

**18. Power to issue regulation and directive**

1/ The House of Peoples' Representatives may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Board may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and various procedures of the Corporation.

**19. Transfer of Rights and Duties**

The rights and obligations of Ethiopian Radio and Television Agency are hereby transferred to the Corporation.

**፳. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

፩/ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፬/፲፱፻፹፯ (እንደተሻሻለ)፤

፪/ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፷፯፣ እና

፫/ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፷፯፡፡

**፳፩. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳ የተደነገገው ቢኖርም የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ (፮) እና (፱)፣ በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፷፯ የቴሌቪዥን ምዝገባና ፈቃድን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እና የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፷፯ በሥራቸው የተዘረዘሩትን ተግባራት በሕግ ሥልጣን የሚሰጠው አካል እስከሚረከብ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**፳፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**20. <u>Repealed laws</u>**

The following laws are hereby repealed:

1/ Ethiopian Radio and Television Agency Proclamation No. 114/1995 (as amended);

2/ Ethiopian Broadcasting Service Proclamation No.15/1975; and

3/ Ethiopian Broadcasting Service Regulations No. 20/1975.

**21. <u>Transitory Provision</u>**

Notwithstanding the provision of Article 20 of this Proclamation, Article 5 (6) and (9) of Ethiopian Radio and Television Agency Proclamation No. 114/1995, provisions of Ethiopian Broadcasting Service Proclamation No. 15/1975 related to registration and licensing of television and Ethiopian Broadcasting Service Regulations No. 20/1975 shall continue to be applicable until a body to be assigned by law overtakes the activities under them.

**22. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of November, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**